## መመሪያ ቁጥር 891/2014

## የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት (ማሻሻያ) መመሪያ

ከጥራጥሬ ግብይት ጋር በተያያዘ ያጋጠሙ ችግሮችን ለመቅረፍ የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት መመሪያ ቁጥር 529/2013ን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር በጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ደንብ ቁጥር 377/2008 አንቀጽ 21 መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት (ማሻሻያ) መመሪያ ቁጥር 891/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ማሻሻያ**

   የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት መመሪያ ቁጥር 529/2013 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

   1/ ከመመሪያው አንቀጽ 13.4 ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (13.5) ተጨምሯል፣

   (13.5) ማንኛውም የግብይት ተዋናይ ከአንድ የምርት ዘመን ያላለፈበት ምርትም ቢሆን በማንኛውም መጠን በክምችት ይዞ ማቆየት የሀገሪቱን የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት የሚያነድፍ ወይም የሚጎዳ መሆኑን በመግለጽ በጥራጥሬ ምርቶች ግብይት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 377/2008 እና በመመሪያ ቁጥር 529/2013 በተገለጸው መሰረት ለወጪ ገበያ መድረክ አቅርቦ መሸጥ እንዳለበት ሚኒስቴሩ በጽሑፍ ባሳወቀው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ተፈጻሚ ማድረግ አለበት፡፡

3. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 2(1) ላይ የተመለከተው ድንጋጌ በተላለፈ ማንኛውም የግብይት ተዋናይ ላይ የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 377/2008 ተፈፃሚ ይሆንበታል፣

4. **የመመሪያው የተፈፃነት**

   ይህ መመሪያ ከግንቦት 5 ቀን 2014 ዓ/ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ፣ ግንቦት 5ቀን 2014 ዓ/ም

ገብረ መስቀል ጫላ
የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስትር